2017

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፕላንና ልማት ቢሮ
AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE PLAN AND DEVELPOPMENT BUREAU

ቁጥር አብክመ/ፕ/ል/343/17

ቀን 12/09/2017 ዓ.ም

**በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት**

በየደረጃው ለሚገኝ የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ

**ባህር ዳር፤**

**ጉዳዩ፡- የዕቅድ አዘገጃጀት መመሪያን ይመለከታል**

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አስፈጻሚ አካላትን እንደገና ማቋቋሚያና ማደራጃ አዋጅ ቁጥር 280/2014 አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ (1) (ሰ) ስር በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የአብክመ ፕላንና ልማት ቢሮ በክልሉ በየደረጃው ያለውን የዕቅድ አዘገጃጀት ወጥነት ለማስጠበቅ ከሚያዚያ 30/2017 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ የሚሆን የዕቅድ አዘገጃጀት መመሪያ አውጥቷል፡፡

በመሆኑም መመሪያዊ በስራ ላይ እንዲውልና በየደረጃው በሚገኝ የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ያለምንም መሸራረፍ ተግባራዊ እንዲያደርጉ እናሳስባለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ደመቀ ቦሩ ባህሩ (ዶ/ር)
የፕላንና ልማት ቢሮ ኃላፊ



ስልክ ☎058-320-80-38 ፖስታ ✉ 1378 Bahir Dar ፋክስ Fax 058-226-39-10 ኢሜይል Email plandevelopment16@gmail.cc
ድህረ ገጽ Website:- http://www.anrsbopd.gov.et:82/

# የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

## የልማት ዕቅድ አዘገጃጀት መመሪያ

**መመሪያ ቁጥር 1/2017 ዓ.ም**

**ሚያዚያ 2017**

**ባህር ዳር**

በክልሉ ውስጥ ከቀበሌ እስከ ክልል ባሉ የአስተዳደር እርከኖች የሚዘጋጁ የልማት ዕቅዶች ይዘታቸው ወጥነት እንዲኖረው እና የጊዜ ሠሌዳቸውም በግልፅ የተቀመጠ በማድረግ ጥራቱ የተጠበቀ እንዲሆን ማድረግ ተገቢነቱ ስለታመነበት፤ ውስን የሆነውን የመንግሥት ሀብትና የህብረተሰብ እውቀትና ጉልበት ከአካባቢው ነባራዊ ሁኔታና ካለው እምቅ የመልማት አቅም ጋር በማጣጣም መስራት እንዲቻል በእቅድ ሂደት ማመቻቸት ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤ በዕቅድ አዘገጃጀት ሂደት በየደረጃው በሚገኙ መዋቅሮችና በዘርፎች መካከል ያለውን ትስስር በማጠናከር የታችኛውን ህብረተሰብና ሌሎች የሚመለከታቸውን አካላት ሁሉ ተሳታፊ በማድረግ የዕቅድ አዘገጃጀት ሥርዓት የሚዘረጋበትን ምቹ ሁኔታ በመፍጠር በዘርፉ የሚስተዋለውን ችግር ለመቅረፍ ጠቀሜታው የጎላ በመሆኑ፤ከቁጥቁጥ በወጣ መልኩ ችግር ፈችና የክልሉን ሕዝብ ፍትሐዊ የመልማትና የልማት ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያስችል የልማት ዕቅድ ማዘጋጀት በማስፈለጉ፣ ከዕቅድ አዘገጃጀት ጋር በተያያዘ ድክመት በሚያሳዩ ተቋማት፣ አመራሮች እና ባለሙያዎች ላይ የማስተካከያ እርምጃዎች መዉሰድ የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፕላንና ልማት ቢሮ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አስፈጻሚ አካላትን እንደገና ማቋቋሚያና ማደራጃ አዋጅ ቁጥር 280/2014 አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ (1) (ሰ) ስር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ ድንጋጌዎች

## 1. አጭርርዕስ

1. ይህ መመሪያ "የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የዕቅድ አዘገጃጀት መመሪያ ቁጥር 1/2017 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. **"ዕቅድ"** ማለት ከክልል እስከ ቀበሌ ባለው ደረጃ የተዘጋጀ የመንግሥት ተቋማት የረጅም ዘመን ወይም የመካከለኛ ወይም የአጭር ጊዜ/ዓመታዊ/ የፖሊሲ

ማስፈጸሚያ ሰነድ ሆኖ ዓላማን የመንደፍ፣ ግብን የመተለም፣ የተግባራትን ቅደም ተከተል የመዘርዘር፣ ስልቶችን የመቀየስና መርሀ ግብር የማውጣት እንዲሁም ዓላማዎችን ለማሳካት የሚያስፈልግ የማስፈፀሚያ ሀብት የመመደብ ሂደት ነው፡፡

2. **"የዕቅድ ኡደት"** ማለት የልማት መልካም አጋጣሚዎችንና ማነቆዎችን የመለየት፣ ዕቅድ የማዘጋጀት፣ የተዘጋጀውን ዕቅድ የመመዘን፣ ዕቅዱን የማጽደቅ፣ የመተግበር፣ የመከታተልና የመገምገም እንዲሁም ትምህርት የመውሰድ ተግባራትን የሚያካትት ነው፡፡
3. **"ግምገማ"** ማለት በመንግሥት ተቋማት የዋና ዋና ተግባራት ውጤታማነት፣ ለውጥ፣ ተገቢነት ዙሪያ በጊዜ ገደብ ተወስኖ የሥራ ደረጃን የመመዘን ሂደት ነው።
4. **"ክትትል"** ማለት የተቋሙ ልዩ ልዩ አካላት የሚመለከታቸውን የሥራ ዘርፍ ከግብዓት፣ ከተግባራትና ከውጤት አኳያ ተከታታይነት ባለው መልኩ ድጋፍ ለመስጠት የሚከናወን ሂደት ነው፡፡
5. **"ቁጥጥር** "ማለት በየደረጃው በሚገኝ ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴ አባላት የሚከናወን ሆኖ ግብረ-መልስ መስጠትንና የተለያዩ የእርምት እርምጃዎች እንዲወሰዱ ማድረግንም የሚያካትት ነው፡፡
6. **"ቢሮ"** ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፕላንና ልማት ቢሮ ነው፡፡
7. **"አስፈፃሚ አካል"** ማለት በክልሉ መንግስት የተቋቋመ ማንኛውም የአስተዳደር ወይም የአስፈጻሚ አካል ወይም የልማት ድርጅት ነው፤
8. **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
9. በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ጾታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ይጨምራል፡፡

## 3. የተፈጻሚነት ወሰን

1/ ይህ መመሪያ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በተቋቋመ ማንኛውም የመንግስት አስፈጻሚ አካል ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እንደተጠበቀ ሆኖ የዕቅድ ተግባራትን በተመለከተ በክልሉ ውስጥ በየደረጃው የተቋቋሙት ምክር ቤቶች በዚህ መመሪያ መሰረት ስራቸውን ማከናወን አለባቸው፡፡

## 4. ዓላማ

መመሪያው የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡፡

1. ሁሉም የልማት ተዋናይ በክልሉ ብሎም በሀገሪቱ የጋራ ርዕይ ላይ እንዲያተኩሩ ለማስቻል፤
2. የመንግሥትን ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማስተግበር፤
3. የዕቅድ ዝግጅት ሥራ ከክልል እስከ ቀበሌ ባለው አደረጃጀት እንዲጠናከር በማድረግ በየደረጃው በሚዘጋጁ ዕቅዶች መካከል የዓላማዎችን አንድነትና ትስስር ለመፍጠር፤
4. ከክልል እስከ ቀበሌ ድረስ ችግር ፈች፣ ደረጃውን የጠበቀ፣ የተቀናጀ፣ ተያያዥነትና ወጥነት ያለው ተመጋጋቢ የዕቅድ ይዘት እንዲኖር ለማድረግ፤
5. በየአስተዳደር እርከኑ የሚዘጋጁ የአጭር፣ የመካከለኛ እና የረጅም ጊዜ ዕቅዶች ተመጋጋቢነትና ተያያዥነት እንዲኖራቸው ለማስቻል፤
6. በየደረጃው የሚዘጋጅ ዕቅድን በተቀመጠው የጊዜ ሠሌዳና በሚፈለገው ይዘት መሠረት ተዘጋጅቶ ወደሚመለከታቸው ውሣኔ ሰጪ አካላት በወቅቱ ለማቅረብና ለማጸደቅ፣
7. በየደረጃው የሚገኙ የሚመለከታቸው አካላት በዕቅድ ዝግጅት ሂደት ሚናቸውን በግልፅ በማመላከት ኃላፊነትና ተጠያቂነት እንዲኖር ለማስቻል ነው፡፡

# ክፍልሁለት

# የዕቅድ አዘገጃጀት ሂደት መርሆዎች፣ አቀራረብና አፀዳደቅ ሥርዓት

## 5. የዕቅድ አዘገጃጀት መርሆዎች

ዕቅድ ሲዘጋጅ ቢያንስ የሚከተሉትን ዋና ዋና መርሆዎች ማሟላት አለበት፡-

1. የረጅም ጊዜ እይታ ያለው መሆን አለበት፡፡ ለዚህም፡-

   ሀ) በበቂና አስተማማኝ መረጃ ላይ በመመሥረት የሚዘጋጀው ዕቅድ ክልሉ ባሉት የልማት ጸጋዎች እና ችግሮቹን በሚፈታ አግባብ የሚዘጋጅ፣ በረጅም ጊዜ ሊሳኩ የሚታሰቡ ዓላማዎችንና አጠቃላይ ክልላዊና አገራዊ አቅጣጫዎችን ግምት ውስጥ የሚያስገባ፣ በተለይም ከ25 ዓመት የአሻጋሪ

ዕድገት እና የዘላቂ ልማት ዕቅድ ጋር ትስስር ያለው፣ የወደፊቱን ሁኔታ በበቂ የሚተነትንና የሚተነብይ፣ ሊመጡ የሚችሉ ለውጦችንና ክስተቶችን ማካተት የሚችል መሆን አለበት።

ለ) የሚዘጋጀው ዕቅድ በዘርፉ ዕውቀት ያላቸውን ባለሙያዎች በመጠቀም ሳይንሳዊና ቴክኒካዊ ሆኖ መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡

2. ዕቅድ ሲዘጋጅ እንዲሳኩ የታሰቡ ግልጽ ዓላማዎች ሊኖሩት ይገባል፡፡ በመሆኑም፡-

ሀ) ዓላማዎች በማያሻማ፣ ግልፅ በሆነና ሁሉም የሚመለከተው አካል ሊረዳው በሚችለው አግባብ መፃፍና መገለጽ ይኖርባቸዋል፤

ለ) ግቡም መነሻና መድረሻ ያለው፣ ሊተገበርና ሊለካ የሚችል እንዲሁም በጊዜ የተገደበ ሆኖ መቀረጽ አለበት።

3. ወጥነትና ተመጋጋቢነትን የጠበቀ መሆን ይገባዋል፡፡ በመሆኑም የተቋማት ዕቅድ እርስ በርስ እና ከክልሉ መሪ ዕቅድ፣ በየአስተዳደር እርከኑ የሚዘጋጁ ዕቅዶች ክልልና ሀገር አቀፍ ዕቅዶች እንዲሁም ከሀገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ስታንዳርዶች ጋር የተሳሰሩና የተመጋገቡ መሆን ይኖርባቸዋል፣

4. የአሠራር ሥርዓትና ቅደም ተከተልን የጠበቀ መሆን አለበት፡፡ ስለሆነም ሁኔታዎችን በሚገባ ከመተንተን ጀምሮ ቅደም ተከተላቸውን በጠበቀ መልኩ ስትራቴጅያዊ ጉዳዮችን፣ የትኩረት መስኮችንና የትኩረት አቅጣጫዎችን፣ ዓላማዎችን፣ ግቦችን፣ ዋና ዋና ተግባራትን፣ የማስፈጸሚያ ስልቶችን፣ የማስፈጸሚያ ሀብትን፣ ስጋቶችንና እሳቤዎችን፣ የክትትልና ግምገማ ስርዓትን እንዲሁም የድርጊት መርሃ ግብርን ያካተተ መሆን ይጠበቅበታል፡፡

5. ዕቅዱ ዓላማዎችን ለማሳካት አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮችን ሁሉ ያካተተ/የያዘ ወይም ምሉዕ መሆን ይኖርበታል፣

ሀ) ከቦታ አንፃር በዕቅዱ መካተት ያለባቸው ቦታዎች/አካባቢዎች መካተት ይገባቸዋል።

ለ) ከይዘት አንፃርም አስፈላጊ ጉዳዮችን የዳሰሰና በዕቅዱ ላይ የተመላከቱ የተለያዩ ክፍሎች እርስ በርሳቸው የሚጣጣሙ መሆን ይኖርባቸዋል።

6. የማስፈፀሚያ ሀብትን መሠረት ያደረገ መሆን አለበት፡፡ በመሆኑም፡-

ሀ) የሚዘጋጀው ዕቅድ በዋናነት ያለውን ከባቢያዊ ፀጋ ወይም እምቅ አቅም በላቀ ደረጃ የሚጠቀም፣ በውስን ሀብት ሊከናወኑ የሚገባቸውን ጉዳዮች ቅድሚያ የሰጠና ቅደም ተከተል ያስቀመጠ መሆን ይኖርበታል፤

ለ) የፊዚካል ዕቅዱ በመንግስት የሚመደብ በጀትን ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን ይኖርበታል፡፡

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ሀ) እና ለ) የተመላከቱ ውስን የዕቅዱ ማስፈጸሚያ ሀብቶችን በቅልጥፍናና በውጤታማነት በአግባቡ በመጠቀም ብክነትን በመቀነስ የላቀ ውጤት እንደሚያመጣ የሚያረጋግጥ ስልት የሚከተል መሆን ይኖርበታል።

መ) አንዱ ሴክተር ለሌላው የሚኖረውን አወንታዊ አስተዋፅኦ መሠረት በማድረግ ዕቅዱ በተለያዩ ሴክተሮችና ክፍላተ ኢኮኖሚዎች መካከል ሊኖር የሚገባውን ትስስር፣ ዝምድናና ተደጋጋፊነት በማሳየት ተቀናጅቶ በመሥራት የሀብት ብክነትንና የሥራ ድግግሞሽን ማስወገድ የሚችልና የላቀ ውጤት ማምጣት የሚችል መሆን ይኖርበታል።

7. የዕቅድ ዝግጅት ሂደቱ አሣታፊ መሆን አለበት፡፡ ስለሆነም፡-

ሀ) የሚዘጋጁ ዕቅዶች ከላይ የመንግስት ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን እንዲሁም የትኩረት አቅጣጫዎችን መነሻ ያደረጉ እንዲሁም ከታች የአካባቢውን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘቡ፣ የህብረተሰቡን ፍላጎት መሠረት ያደረጉ እና ማህበረሰቡን እና የሚመለከታቸውን አጋር አካላት ያሳተፉ መሆን የሚጠበቅባቸው በመሆኑ ከላይ ወደታች እና ከታች ወደ ላይ ያሉትን የአስተቃቀድ ስልቶች ያመጣጠኑ ሊሆኑ ይገባል።

ለ) ሁሉም የማህበረሰብ አባላት በየደረጃው በሚደረጉ የልማት እንቅስቃሴዎች /ለውጦች ንቁ ተሳትፎ ማድረግ የሚገባቸው ሲሆን በተለይም በልማት እንቅስቃሴዎች ተጠቃሚ ያልሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች /ሴቶች፣ ህጻናት፣ ወጣቶች፣ አረጋውያን፣ የኤች አይቪ ኤድስ ህሙማንና ለዚሁ የተጋለጡ የህብረተሰብ ክፍሎች፣ አካል ጉዳተኞች...ወዘተ/ እና አጋር አካላት በዕቅድ ዝግጅት ሂደቱ በተገቢው የሚያሳትፍ በሂደቱም አቅም የሚገነባና የባለቤትነት መንፈስ የሚፈጥር እንዲሁም ፍትሃዊ በሆነ መልኩ የዜጎችን የልማት ፍላጎት የሚያሟላ እና መብታቸውን የሚያረጋግጥ መሆን

ይኖርበታል። በተለይም ልማት በመንግስት በጀትና ጥረት ብቻ የሚመጣ ባለመሆኑ ይልቁንም ህዝቡን ማነቃነቅና ለልማት ማሰለፍ ተገቢና አስፈላጊ በመሆኑ በታችኛው አስተዳደር ዕርከን የሚዘጋጅ ዕቅድ የአካባቢውን እምቅ አቅም እንዲሁም ህዝቡን በማነቃነቅ እውቀትና ጉልበት በአግባቡ መጠቀም በሚያስችል መልኩ አሣታፊ መሆን ይኖርበታል፡፡

8. ዕቅዱ የህዝብ ዕቅድ በመሆኑ አጠር ባለና በቀላሉ ሁሉም ሊረዳውና ሊተገብረው በሚችል አቀራረብ መዘጋጀት ይኖርበታል

## 6. የዕቅድ ዝግጅት መነሻዎች

የሚከተሉት ነጥቦች ለዕቅድ ዝግጅት መነሻ መሆን አለባቸው፡፡

1. በዕቅድ ዝግጅት ሂደት ከወቅታዊ ሁኔታዎች እንዲሁም ከአገሪቱ እና ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ የመንግሥት የትኩረት የትኩረት መስኮችንና አቅጣጫዎችን የቃኘ መሆን አለበት፣
2. በየደረጃው የሚዘጋጀው የልማት ዕቅድ ከመንግስት የልማት ፍላጎትና አቅጣጫ የሚመነጭ እንደመሆኑ መጠን የመንግስት ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን እንዲሁም የተለያዩ አዳዲስ አሰራሮችን/Initiatives/ መሠረት አድርጎ መዘጋጀት አለበት፣
3. ከሀገራችን ፖሊሲ፣ ስትራቴጅና የልማት ቅደም ተከተል ጋር በተጣጣመ መንገድ እንዲተገበሩና ክልላችን ኃላፊነቱን በአግባቡ እንዲወጣ በሚደረገው ጥረት በየአስተዳደር እርከኑ የሚገኝ አካል ሁሉ ድርሻውን መውሰድ ስለሚገባው ዘላቂ የልማት ግቦችን በዕቅድ ዝግጅት ሂደት ከግምት ውስጥ በማስገባት አካቶ ማቀድ ተገቢ ነው፣
4. የሴቶችን፣ የህጻናትን፣ የወጣቶችን፣ የአረጋውያንን፣ የአካል ጉዳተኞችን፣ የአካባቢ ጥበቃን እና ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ የመገንባት ስትራቴጅን፣ የስነ ህዝብን፣ የኤች አይቪ ኤድስን፣ ...ወዘተ ዘርፈ-ብዙ ጉዳዮች ከተጠቃሚነትና ተሳታፊነት አኳያ በዕቅዱ ውስጥ ተገቢውን ትኩረት አግኝተው መካተት አለባቸው፣

5. ለዕቅድ ዝግጅት የሚያገለግሉ ጥናቶችና ከመጀመሪያ እና ከሁለተኛ የመረጃ ምንጭ የሚሰበሰቡ ጥሬ መረጃዎች ተአማኒነትና አግባብነት ያላቸው፣ ግልጽና ለአጠቃቀም ቀላል የሆኑ፣ አዋጭ እና ወቅታዊ መሆን አለባቸው፡፡

## 7. በዕቅድ ሊካተቱ ስለሚገባቸው ጉዳዮች፣ ዕቅድን ስለመመዘን፣ ስለመተግበርና ስለመከታተል

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 የሰፈሩት አጠቃላይ አገላለጾች እንደተጠበቁ ሆነው በዕቅድ ዑደት ውስጥ የሚያልፉ ዝርዝር ተግባራት በቅደም ተከተል የሚከተሉት መሆን አለባቸው።

1. እያንዳንዱ አስፈጻሚ የመንግሥት ተቋም በሕግ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት መሠረት አድርጎ በዕቅድ ዝግጅት ሂደት ውስጥ የመጀመሪያው ተግባር የክልሉን ወይም የዞኑን፣ የወረዳውን ወይም የከተማ አስተዳደሩን ወይም የቀበሌውን ዋና ዋና የልማት ችግሮችና መንስዔዎች የመለየትና ያለውን እምቅ ሃብት መረጃ የማሰባሰብና በበቂ ሁኔታ የመተንተን ስራ መሥራት አለበት፤
2. የዕቅድ ዝግጅት ወይም ቀረፃ ሂደት የዕቅድ ሰነዱ የሚዘጋጅበትና ቅርፅ የሚይዝበት ደረጃ ሲሆን ፀጋዎችንና ሀብቶችን ለመጠቀምና ችግሮችን ለማስወገድ የሚያስችል የልማት ዓላማ እና ግብ በማስቀመጥ ወደ ዓላማ የሚያደርሱ መንገዶችንና የሚከናወኑ የተግባራትን ዓይነትና መጠን በመለየት ከማስፈፀሚያ ሀብት ጋር በማጣጣም መወሰንን የሚያጠቃልል መሆን አለበት።
3. የዕቅድ ምዘና በዕቅድ አቅራቢው አካል የቀረበው የልማት ዕቅድ ብቃት የሚፈተሽበት ሂደት ሲሆን የተዘጋጀው የልማት ዕቅድ ዓላማና ግብ ለአካባቢው ተስማሚና ተግባራዊ የመሆን ዕድሉ እና የተነደፉት ስልቶችና የስራ ዝርዝሮች ወደ ታለመላቸው ዓላማና ግብ የሚያደርሱ ስለመሆናቸው ሥልጣን የተሰጠው ክፍል(የተቋሙ ማኔጅመንት፣ በተጠቃሚና አጋር አካላት፣ በየደረጃው ባለ የፕላንና ልማት ቢሮ መዋቅር፣ በካቢኔ እና በህዝብ ተወካዮች/ቋሚ ኮሚቴ/) የሚመዝንበት ሂደት ሆኖ የሚከተሉት ጉዳዮች በመመዘኛነት ከሚያገለግሉ ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡
   ሀ) የዓላማውና የግቡ ግልጽነት፤
   ለ) የቀረቡት የሥራ ዝርዝር ሁኔታዎች፤
   ሐ) ለመፈጸም ያለው የሰው ኃይልና ብቃት፤

መ) ያለው የበጀት አቅም፤

ሠ) ልማቱ ለህብረተሰቡ የሚሰጠው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ

የሚሉት ናቸው።

4. የዕቅድ ማጽደቅ ሂደት ከዕቅድ ምዘና በኋላ የሚተገበር ሲሆን በዕቅድ ምዘና ወቅት የተሰጡ ገንቢ አስተያየቶች እንዲካተቱ በማድረግ ዕቅዱ በመጨረሻ የታሰበውን ዓላማና ግብ ያሳካል ተብሎ ሲታመን በቀበሌ፣ በወረዳ፣ በዞን እና በክልል ደረጃ በካቢኔ አባላትና በመጨረሻም በምክር ቤት ፀድቆ ወደ ተግባር የሚገባበት ደረጃ ነው፡፡
5. የዕቅድ ትግበራ ደረጃ የሚመለከታቸው ፈፃሚ አካላት የፀደቀውን የልማት ዕቅድ መሠረት አድርገው የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት የፊዚካል ዕቅዱን ከተፈቀደው በጀት ጋር በማጣጣም ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ የሚገቡበት ሂደት ነው፡፡
6. የክትትል፣ ቁጥጥርና ግምገማ ስርዓት የልማት ዕቅድ ተግባራዊ በሚደረግበት ጊዜ የታለመው ዓላማና ግብ በታሰበለት አቅጣጫ እየሄደ መሆኑን በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ፣ በተገመተው የማስፈጸሚያ ሀብት አንፃር መከናወኑን ለማረጋገጥ እንዲሁም ቀልጣፋና አጥጋቢ ውጤቶችን ለማግኘት የሚያስችል ሥርዓት ነው።

## 8. የዕቅድ ዝግጅት ቅደም ተከተል

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ (2) የሰፈረው ጠቅላላ አገላለጽ እንደተጠበቀ ሆኖ ዕቅድ ለማዘጋጀት በመጀመሪያ ደረጃ ለማቀድ ማቀድ እና በቂ ቅድመ ዝግጅት ማድረግ ዕቅዱ ጥራቱን የጠበቀና ችግር ፈቺ ሆኖ እንዲዘጋጅ ከማድረግ አንፃር ትልቅ ሚና ስለሚኖረው ዕቅዱ በማን እንደሚዘጋጅ ማሰብና አደረጃጀት መፍጠርን፣ በምን ያህል የጊዜ ገደብ እንደሚከናወን መወሰንን፣ እንዲሁም ለሥራው አስፈላጊ ሀብት መመደብን፣ ለዕቅድ ዝግጅት ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎችን ማደራጀትንና እንደ ሁኔታውም ጥናት ማካሄድን ማካተት አለበት፡፡
2. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 እና በአንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ(1) የሰፈረው ጠቅላላ አገላለጽ ቢኖርም በየደረጃው በሚገኘው በፕላንና ልማት ቢሮ አደረጃጀት የሚዘጋጀው የተጠቃለለ ዕቅድም ይሁን ተቋማት ወደ ፕላንና ልማት ቢሮ እና

በየደረጃው ወደ ሚገኙ መዋቅሮቹ የሚልኩት ዕቅድ ሲዘጋጅ ሊያካትታቸው የሚገቡ ዋና ዋና ነጥቦች በቅደም ተከተል የሚከተሉት መሆን አለባቸው፡-

**ሀ) የሁኔታዎች ትንተና፡-** በማካሄድ የየዘርፉ የልማት ዕድሎችና መልካም አጋጣሚዎች ምን እንደሆኑ በበቂ ሁኔታ መተንተን፣ ያለፉት ዓመታት አፈፃፀም ሁኔታና አዝማሚያ እንዲሁም በዋና ዋና አመላካቾች ሴክተሩ ያለበትን ደረጃ ማብራራት፣ የሚታዩ ጥንካሬዎችን፣ ድክመቶችን፣ ችግሮችን/ማነቆዎችን መለየትና የቀጣይ አቅጣጫዎችን ማመላከት፤

**ለ) ርዕይ፣ ተልዕኮና ዕሴቶችን ማስቀመጥ፡-** ለመካከለኛና ለረጅም ዘመን ዕቅድ ግዴታ ሆኖ ለዓመታዊ ዕቅድ ግን ግዴታ አይደለም፡፡

**ሐ) የዕቅዱን መነሻዎች ማስቀመጥ፡-** በተለይም የመንግሥት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ፣ የአገሪቱ ርዕይ /የክልሉ፣ የተቋሙ ርዕይ/ ፣ ያለፉት ዓመታት ዕቅድ አፈፃፀም፣ የሕዝቡ አዳዲስ ፍላጐቶችና ጥያቄዎች፣ በፌደራል ደረጃ የተዘጋጀ ዕቅድ ፣ ሀገሪቱ የፈረመቻቸው ዓለም አቀፍና አህጉር አቀፍ ዕቅዶች፣ ልዩ ልዩ ጥናቶችና መረጃዎች፣ ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች የዕቅዱ መነሻዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

**መ) ስትራቴጅክ ጉዳዮችን ማስቀመጥ፡-** ከጥንካሬ ድክመት መልካም አጋጣሚና ስጋት ትንተና ከተገኙ መረጃዎች ስትራቴጂያዊ ጉዳዮችን በመለየት ማስቀመጥ ተገቢ ይሆናል፡፡

**ሠ) የትኩረት መስኮችን ማስቀመጥ፡-** አንኳር የሆኑ የርብርብ ማዕከላት ምን እንደሆኑ አጠር ባለ መልክ ማመላከትና የትኩረት መስኮችን መለየት፤

**ረ) የትኩረት አቅጣጫዎችን ማስቀመጥ፡-** እነዚህ ወደ ሚፈልገው ውጤት ለመድረስ ሁሉም ትኩረት የሚያደርግባቸውና የሚመራባቸው አቅጣጫዎች /directions/ ናቸው፡፡ እነዚህም ከፖሊሲዎች፣ ከስትራቴጅዎች፣ ከትኩረት መሰኮች፣ ከሶሸዮ-ኢኮኖሚ ማዕቀፎች፣ ካለው ነባራዊ ሁኔታ፣ ወዘተ.... የሚነሱ ሆኖ ዓላማውን ለማሳካት የሚቀመጡ አቅጣጫዎች ናቸው፡፡

**ሰ) ዓላማ በመንደፍ፣ ግብ በመተለም እና ዋና ዋና ተግባራትን በመዘርዘር** አንድን ዓላማ ለማሳካት ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ግቦች በዓላማው ሥር በማካተት እያንዳንዱን ግብ ሊያሳካ በሚያስችል ሁኔታና ትስስሩን በጠበቀ መልኩ ዋና ዋና ተግባራትን መዘርዘር፤

**ሸ) ስትራቴጂያዊ የማስፈጸሚያ ስልቶች** በዕቅዱ የተቀመጡ ዓላማዎችንና ግቦችን ለማሳካት የምንከተላቸውን መንገዶች ከጊዜ፣ ከማስፈፀሚያ ሀብት እና ከመሳሰሉ ጉዳዮች አንፃር

ሲመዘኑ አዋጭነታቸውን የሚያረጋግጡ ሲሆኑ የምንከተላቸው ስልቶች ልንደርስ ወደ ምንፈልገው የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደረጃ ወይም ልናሳካው ወደምንፈልገው ዓላማና ግብ ለመድረስ የሚያስችሉ እንዲሆኑ ማድረግ፤

**ቀ) የማስፈፀሚያ ሀብትን** በመወሰን በፊዚካል ዕቅዱ ለተቀመጡ ተግባራት ማስፈፀሚያ በቂ በጀት እንዲመደብ በማድረግ የበጀት ምንጩንም /ከማህበረሰቡ የሚገኝ የገንዘብ፣ የጉልበትና የቁሳቁስ አስተዋጽኦን ጨምሮ/ ማመላከት የሚገባ ሲሆን በፊዚካል ዕቅዱ የተቀመጡ ዓላማዎችና የትኩረት መስኮች ለማስፈፀሚያ ሀብት አመዳደብ/ድልድል መሠረት የሚጥሉ እንደመሆኑ መጠን የፊዚካል ዕቅዱ ቀደም ብሎ ተዘጋጅቶ ከማስፈፀሚያ ሀብቱ/በጀት/ ጋር እንዲጣጣም ማድረግ፤

**በ) ስጋቶችንና እሳቤዎችን በመለየት** በዕቅድ ዘመኑ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ስጋቶችን በመተንበይና የእነዚህን ስጋቶች ተጽእኖ እንዴት መቀነስ እንደሚቻል ስልት በመንደፍ እንዲሁም ምን ምን ጉዳዮች እሳቤ ውስጥ መግባት እንዳለባቸውና ከዚህ አንፃር ምን መሠራት እንዳለበት ጭምር አስቀድሞ በዕቅድ ማመላከት፣

**ተ) የክትትልና ግምገማ ሥርዓት** በመዘርጋት ክትትልና ግምገማው በምን ዘዴ እንደሚደረግ፣ መቼ ወይም በምን ያህል የጊዜ ርዝመት እንደሚከናወን፣ በሂደቱ ተሳታፊ አካላት እነማን ሊሆኑ እንደሚችሉ በግልፅ በዕቅድ ሰነዱ ማመላከት፤

**ቸ) የድርጊት መርሃ ግብር** በማዘጋጀት የተዘጋጀውን ዕቅድ ወደ ተግባር ሊያሸጋግርና ተጠያቂነትን ሊያሰፍን በሚያስችል መልኩ ምን ሥራ መቼ እንደሚሠራ፣ ለተግባሩ ኃላፊነት የተሰጠው አካል ማን እንደሆነ፣ ከተግባሩ ጋር ተነፃፃሪነት ባለው መልኩ የተመደበው ጥቅል በጀት ተሸንሽኖ በጊዜ መመላከት ይኖርበታል።

## 9. የዕቅድ ሰነድ አቀራረብና አፀዳደቅ ሂደት

1. በየደረጃው የሚገኝ የቢሮው አደረጃጀት በሚልከው የዕቅድ ጥሪ መሠረት ተቋማት ደረጃውን የጠበቀ ዕቅድ አዘጋጅተው በትይዩ ለሚገኝ የቢሮው መዋቅር በወቅቱ መላክ አለባቸው፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ተቋማት የሚልኩት መነሻ ዕቅድ በመሪ ዕቅድ አስተቃቀድ ፎርማት መሠረት መሆን አለበት።

3. የሚዘጋጀው ዕቅድ ቢያንስ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 የተጠቀሱ ጉዳዮችን ማካተት አለበት፡፡
4. ዕቅዱ በዚህ መመሪያ መሠረት የተዘጋጀ መሆኑ ከተረጋገጠና በተቋሙ ማኔጅመንት ከተገመገመ በኋላ በተቋሙ ኃላፊ/ምክትል ተፈርሞ መላክ አለበት፡፡
5. ዕቅዱ የተላከለት በየደረጃው የሚገኝ የፕላንና ልማት ቢሮ መዋቅርም በማክሮ ደረጃ ያሉ ጉዳዮችን በመተንተንና ከተቋማት የደረሰውን ዕቅድ በግብዓትነት በመጠቀም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተገለጸው መሠረት ዋና ዋና ጉዳዮችን አካቶ የተጠቃለለ ዕቅድ አዘጋጅቶ ለካቢኔ በማቅረብ ከውይይት በኋላ በሚመለከተው ምክር ቤት ይሁንታ አግኝቶ መጽደቅ አለበት፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) የተገለጸው ቢኖርም ከብሔረሰብ አስተዳደር ዞኖች እና ከተማ አስተዳደሮች በስተቀር በዞን የአስተዳደር እርከን ዕቅዱ በካቢኔው እንዲፀድቅ ይደረጋል፡፡

## ክፍል ሶስት

## በዕቅድ ዝግጅት ሂደት የልዩ ልዩ አካላት ሚና፣ ግንኙነት እና የዕቅድ ማቅረቢያ የጊዜ ሠሌዳ

### 10. ዩኒቨርሲቲዎች፣ የምርምር ተቋማትና የምሁራን ማህበር ሚና

1. ለዕቅድ በግብዓትነት የሚውሉ ጥናቶችንና መረጃዎችን ያወጣሉ፤
2. በዕቅድ ዝግጅት ሂደት የተለያዩ ሥልጠናዎችን የመስጠትና የማማከር ሚና ይኖራቸዋል፤
3. በሚመለከታቸው የመንግሥት ተቋማት የሚጠየቁ ሌሎች ከሥራቸው ጋር አግባብነት ያላቸው ድጋፎችን ያደርጋሉ፡፡

### 11. በየደረጃው የሚገኙ አስፈጻሚ ተቋማት ሚና፡-

1. የየተቋማቸውን መረጃ ያሰባስባሉ፣ ያደራጃሉ፣ ይተነትናሉ፣ ለተጠቃሚዎችም ያሠራጫሉ፤
2. በዕቅድ ዝግጅት ዙሪያ በተዋረድ ላሉ አካላት ስልጠናና የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ያከናውናሉ፣

3. ከፕላንና ልማት ቢሮ እና በየደረጃው ካሉ መዋቅሮቹ በተላከላቸው የዕቅድ ጥሪ መሠረት በተዋረድ ላሉ አካላት የዕቅድ መነሻዎችንና አቅጣጫዎችን ይሰጣሉ፣ ከታች የሚመጣውን መነሻ ዕቅድ መሠረት አድርገው የየራሳቸውን ዕቅድ ያዘጋጃሉ፣ የተዘጋጀውን ዕቅድ ለእናት መ/ቤታቸውና በየደረጃው ላለ የፕላንና ልማት ቢሮ መዋቅር በወቅቱ ይልካሉ፡፡
4. የረጅም፣ የመካከለኛ እና የአጭር ጊዜ መነሻ ዕቅድ በተሟላ እና ጥራት ባለው መልኩ አዘጋጅተው በየደረጃው ላለ የፕላንና ልማት ቢሮ አደረጃጀት በወቅቱ ያቀርባሉ፡፡
5. በየደረጃው ባለ የፕላንና ልማት ቢሮ መዋቅር የተጠቃለለ ዕቅድ ከተዘጋጀና በውይይት ዳብሮ በሚመለከተው አካል ከጸደቀ በኋላ እንደማዕቀፍ ሆኖ ከሚያገለግለው መሪ ዕቅድ ጋር ተናባቢ እንዲሆን ከማድረግ አንጻር ተቋማት እንደ አስፈላጊነቱ የየራሳቸውን መነሻ ዕቅድ ማሻሻልና የመጨረሻ ቅርጽ እንዲይዝ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡
6. በዕቅድ ዝግጅት ሂደት ህብረተሰቡንና አጋር አካላትን ማሳተፍና አስተባብሮ መምራት ይኖርባቸዋል፡፡ በተለይ በቀበሌ ደረጃ በሚዘጋጀው ዕቅድ ማህበረሰቡ ዋነኛ ተዋናይና ባለቤት መሆን ይኖርበታል፡፡ ለልማቱ የላቀ አበርክቶ የሚደርግበት ሁኔታ መመቻቸት ይኖርበታል፡፡
7. ለዕቅድ ዝግጅቱ ትኩረት በመስጠት ብቃት ያለው መዋቅር መዘርጋትና እንደ እፈላጊነቱ በቂ አደረጃጀት መፍጠርና ብቁ ባለሙያ መመደብ እንዲሁም የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት ይኖርባቸዋል፡፡
8. ተቋማት የየሴክተራቸውን ዕቅድ የማሳተም፣ የማሰራጨትና የዕቅድ ትውውቅ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

## 12. የቢሮው ሚና

1. እንደ አስፈላጊነቱ የክልሉን የማክሮ ኢኮኖሚ እና ፊስካል ማዕቀፍ ያዘጋጃል፡፡
2. በየደረጃው የሚገኝ የፕላንና ልማት ቢሮ መዋቅር፡- ዕቅድ ዝግጅትን በተመለከተ በየደረጃው ለሚገኙ የመንግሥት ተቋማት የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን ይሰጣል፡፡
3. የተጠቃለለ የማህበራዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊ፣ መልክዓ ምድራዊ እና የስነ ህዝብ መረጃ ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል፣ ፖሊሲዎችን ይተነትናል እንደአስፈላጊነቱ ክልላዊ የሆኑ

ፖሊሲዎችን ይነድፋል፣ ወቅታዊ የሆነ ክልላዊ የሀብት ግመታ መረጃም ያዘጋጃል፡፡ የማክሮ ኢኮኖሚና ክፍላተ ኢኮኖሚ አመልካቾችንና መመዘኛዎችን፣ ያዘጋጃል፣ አሠራሮችን ይቀርጻል፡፡

4. የመንግሥት አስፈጻሚ ተቋማት ዕቅዳቸውን እንዴት አዘጋጅተው በምን ያህል የጊዜ ገደብ ውስጥ መላክ እንዳለባቸው የዕቅድ ጥሪ ይልካል፤
5. በማክሮ ደረጃ የተነተነውን እና ከመንግሥት አስፈጻሚ ተቋማት የደረሰውን መነሻ ዕቅድ አጣጥሞ በማጠቃለል እንዲሁም መድረክ በመፍጠርና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመወያየት ዕቅዱን በማዳበር ለአስተያየት ለመስተዳድር ምክር ቤት እንዲደርስ በማድረግ በውይይት የዳበረው ዕቅድ በምክር ቤት እንዲጸድቅ ያደርጋል፡፡
6. ዕቅዱ እንደ ሁኔታው በምክር ቤት ወይም በመስተዳድር ምክር ቤት ከፀደቀ በኋላ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርስ ያደርጋል።
7. ባለፈው በጀት ዓመት የተዘጋጀውን ዕቅድ በመገምገምና በመመርመር ለቀጣይ የዕቅድ ሥርዓት መሻሻል ይረዳ ዘንድ የእያንዳንዱን ተቋም ዕቅድ በተመለከተ በድክመትና በጥንካሬ የታዩ ጉዳዮችን ያካተተ ግብረ መልስ ይሰጣል፡፡
8. የተጠቃለለውን ክልላዊ ዕቅድ የማሳተም፣ የማሰራጨትና ለሚመለከታቸው አካላት የዕቅድ ትውውቅ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

## 13. የገንዘብ ቢሮ ሚና

1. የክልሉ የኢኮኖሚ ዕድገትና ልማት ዘላቂና የተረጋጋ እንዲሆን የሚያስችሉ የፊሲካል ፖሊሲና ስልት ያመነጫል፣ ሥራ ላይ ያዉላል፣ አፈጻጸማቸዉን ይከታተላል፤
2. የተመደበውን በጀት ውጤታማ ሊያደርግ በሚችል መልኩ በልማት ዕቅዱ ቅድሚያ የተሰጣቸውን ጉዳዮችና ዘርፎች በመለየት በጀት ይደለድላል፡፡
3. የበጀት አጠቃቀሙን በተናጠልም ሆነ በጋራ ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ ብክነት በሚያደርሱ አካላት ላይም ተጠያቂነት እንዲኖር ያደርጋል፡፡

## 14. የመስተዳድር ምክር ቤቶች ሚና

1. በየደረጃው ያለ የአስተዳደር ምክር ቤት መድረክ በመፍጠርና ዕቅዱን በማዳበር በምክር ቤት እንዲፀድቅ ያደርጋል፤
2. ምክር ቤት በሌላቸው የአስተዳደር እርከኖች ዕቅዱ በራሱ በመስተዳድር ምክር ቤቱ እንዲፀድቅ ያደርጋል፤
3. በዚህ መመሪያ መሠረት የመንግስት አስፈፃሚ አካላት የተቋማቸውን እና የተጠሪ ተቋሞቻቸውን የልማት ዕቅድ አሠራርና አደረጃጀት እንዲያሻሽሉ፣ እንዲያጠናክሩ እና አስፈላጊውን የሰው ኃይል እንዲያሟሉ አመራር ይሰጣል፤

## 15. የምክር ቤቶች ሚና

1. በየደረጃው የሚገኙ ምክር ቤቶች የአስፈፃሚው ዕቅድ ችግር ፈችና ፋይዳ ያለው ሆኖ በትክክል ስለመታቀዱ ቁጥጥር ያደርጋሉ፣ አስፈላጊ የሆነ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋሉ፤
2. በአስተዳደር ምክር ቤቱ ይሁንታ አግኝቶ የቀረበን ረቂቅ የተጠቃለለ/መሪ ዕቅድ መርምረው ያፀድቃሉ።

## 16. የፕላንና ልማት ቢሮ ከፌደራል የፕላንና ልማት ሚኒስቴር ጋር ስላለው የሥራ ትብብር

1. በሥልጠና፣ በክትትልና ድጋፍ ሥራዎች፣ በመረጃና ተሞክሮ ልውውጥ፣ በጥናትና ምርምር ሥራዎች... ወዘተ በቅርበት፣ በቅንጅትና በትብብር የሚሰራ ይሆናል፤
2. በክልል ደረጃ ለሚዘጋጁ ዕቅዶች የፌደራል ፕላንና ልማት ሚኒስቴር ትብብር ያደርጋል፤
3. የሚዘጋጀው የልማት ዕቅድ አገራዊ ፖሊሲን መሠረት አድርጎ የሚዘጋጅ በመሆኑ በክልል ደረጃ ለሚዘጋጁ ዕቅዶች መነሻ አቅጣጫ ከብሔራዊ የፕላንና ልማት ሚኒስቴር የሚወሰድ ይሆናል፤
4. ማዕከላዊ ስታትስቲክስ አገልግሎት በጥናት የሚያመነጫቸው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ መረጃዎች ለክልሉ የዕቅድ ዝግጅት በግብዓትነት የሚውሉና

ለተጠቃሚዎች የሚሰራጩ ይሆናል፡፡ ስለሆነም አገልግሎቱ ወቅታዊና አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች በማመንጨት ተደራሽ እንደሚያደርግ ይጠበቃል፡፡

## 17. የዕቅድ ዝግጅት የጊዜ ሠሌዳ

1. በዕቅድና በጀት ዑደቱ መሠረት በየደረጃው የሚገኝ እያንዳንዱ ተቋም ከየካቲት ወር ጀምሮ ለዕቅድ ዝግጅት ግብዓትነት የሚውሉ የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን ማለትም የመረጃ መሰብሰብ፣ የማደራጀትና የመተንተን፣ ክፍተቶችን የመለየት ወዘተ ስራዎችን ያከናውናል፡፡ በኋላም የበጀት ዓመቱ 9 ወራት እንደተጠናቀቁ ከሚያዚያ ወር ጀምሮ የበጀት ዓመቱን 9 ወራት አፈጻጸም በመገምገምና ከዚህ ተነስቶ አጠቃላይ የበጀት ዓመቱን አፈጻጸም በመተንበይ የሁኔታዎች ትንተና በማድረግ የቀጣዩን በጀት ዓመት መነሻ ዕቅድ ያዘጋጃሉ።
2. በክልል ተቋማት የሚዘጋጀው ዓመታዊ ዕቅድ ተጠናቆ እስከ ግንቦት 30 ለፕላንና ልማት ቢሮ እና በየደረጃው ለሚገኝ የቢሮው መዋቅር መድረስ አለበት፡፡ የረጅምና የመካከለኛ ዘመን ዕቅድ የሚዘጋጅበትና የሚቀርብበት ጊዜ በዕቅድ ጥሪው መሰረት የሚወሰን ይሆናል፡፡
3. የክልል አስፈጻሚ አካላት በተዋረድ ካሉ ተቋሞቻቸው ዕቅድ የሚቀበሉበትን ጊዜ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2ን በማይቃረን መልኩ በራሳቸው አሰራር ይዘረጋሉ፡፡
4. ቢሮው እና በየደረጃው የሚገኙ የቢሮው መዋቅሮች በበጀት ዓመቱ መጠናቀቂያ ላይ የቀጣዩን በጀት ዓመት ክልላዊ መሪ የልማት ረቂቅ ዕቅድ በማጠቃለል እንዲጸድቅ ለሚመለከተው አካል መላክ ወይም ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
5. የየዕቅድ ዘመኑ የፊዚካል ዕቅድና የማስፈጸሚያ በጀት በአንድ ላይ መጽደቅ ይኖርበታል፡፡

# ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 18. የዕቅድ ክለሳ ስለማድረግ

1. አሳማኝ በሆነ እና በበቂ ማስረጃ በማስደገፍ በሚቀርብ ጥያቄ መነሻነት በየደረጃው ለሚገኝ የፕላንና ልማት ቢሮ መዋቅር ቀርቦ እና በሚመለከተው ውሳኔ ሰጭ አካል ሲፈቀድ ብቻ ዕቅድን መከለስ ይቻላል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለሚቀርቡና በቢሮው በኩል ተቀባይነት ከሚኖራቸው የዕቅድ ክለሳ ምክንያት ከሚሆኑት መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-
   ሀ) የፖሊሲ፣ የስትራቴጅ፣ የደንቦችና መመሪያዎች መለዋወጥ፤
   ለ) የጊዜ ተጽዕኖ፤
   ሐ) የበጀት/የገንዘብ እጥረት
   መ) ተጨማሪ በጀት/ገንዘብ መገኘት፤
   ሠ) በተቋማት የሚደረጉ የመዋቅር ለውጦች፤
   ረ) ተቋማት ሲዋሀዱ ወይም ሲነጠሉ፤
   ሰ) በተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ምክንያት እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተከለሰ ረቂቅ ዕቅድ በየደረጃው ለሚገኝ ካቢኔ እና ምክር ቤት ቀርቦ ካልጸደቀ ተቀባይነት የለውም፤

### 19. የቢሮውና የሌሎች አስፈጻሚ ተቋማት የጋራ ተግባር

1. ዕቅዱን አጠቃሎ በማጠናቀቅ የማሳተምና የማሰራጨት ሥራ በየደረጃው የሚገኙ አስፈጻሚ ተቋማትና የፕላንና ልማት ቢሮ እንዲሁም በየደረጃው የሚገኝ የፕላንና ልማት ቢሮ መዋቅር የጋራ ተግባር ይሆናል።
2. የጸደቀውን ዕቅድ ወደተግባር ለማስገባትና ኃላፊነትና ተጠያቂነት ለመስጠት እንዲቻል ለሚመለከታቸው አካላት ሁሉ በተቋማትና በቢሮው በኩል የዕቅድ ትውውቅ መደረግ አለበት፡፡

### 20. ስለተጠያቂነት አሠራር

1. በዚህ መመሪያ የተገለጹ ሁኔታዎችን በሚያጓድሉ አካላት ላይ ቢሮው እና የተዋረድ መዋቅሩ በሚሰጠው ግብረመልስ ጉድለቶችን እንዲያስተካክሉ መገለጽ ይኖርበታል፤
2. በቢሮው እና በተዋረድ መዋቅሩ የሚሰጠው ግብረመልስ ኃላፊዎችን ወይም ባለሙያዎችን በግልጽ ሊያስተምርና አቅማቸውን ሊያጎለብት የሚችል ድጋፍ መሆን ይኖርበታል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሠረት የማያስተካክል ከሆነ ጉዳዩ በካቢኔ በአጀንዳነት እንዲቀርብና ውሳኔ እንዲሰጥበት ይደረጋል።
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) በተሰጠ ውሳኔ የማይታረም ሆኖ ከተገኘ በየደረጃው ያለ ምክር ቤትና ቋሚ ኮሚቴም ቁጥጥር በማድረግ አስፈላጊ ነው የሚለውን እርምጃ ሊወስድ ይችላል።

## 5. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

ይህን መመሪያ የሚቃረን ማናቸውም ሌላ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

## 6. መመሪያውን ስለማሻሻል

ቢሮው መመሪያውን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ባገኘው ጊዜ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

## 7. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በቢሮው ጸድቆ ከወጣበት **ከሚያዚያ 30 ቀን** 2017 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**ባህር ዳር**

ሚያዚያ 30 ቀን 2017 ዓ.ም

ደመቀ ቦሩ ባህሩ (ዶ/ር)

የአብክመ ፕላንና ልማት ቢሮ ኃላፊ